# የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ

# የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናት፣ አፈቃቀድ እና አፈፃፀም መመሪያ

## 408/2013

**ነሐሴ 2000 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ማ ው ጫ


**ገጽ**

1. መግቢያ---------------------------------------------------------------- 3

**ክፍል 1**

2.ጠቅላላ ---------------------------------------------------------------- 4

3.የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ መፈጸም የሚገባቸው ዋና ዋና ተግባራት ------------------------------------------------------- 5

4 የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች አጠናን ስልት ----------------------------- 9

5. የውሳኔ አሰጣጥ ------------------------------------------------------ 11

**ክፍል 2**

6. ልዩ ትኩረት ስለሚሰጣቸው ሠራተኞች------------------------------ 13

**ክፍል 3**

7. የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መረጃዎች ስለመመዝገብና ስለመያዝ ---------------------------------------------- 14

8. የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት መረጃዎችን ለኤጀን ሲው ሪፖርት ስለማቅረብ -------------------------------------------------------

**ክፍል 4**

9. አውጭው ባለሥልጣን --------------------------------------------- 14

10. የተሻረ መመሪያ------------------------------------------------------ 14

11. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን ------------------------------------ 14

12. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ -------------------------------------- 15

13. አባሪዎች ------------------------------------------------------------ 16

## 1. መ ግ ቢ ያ

የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ከሥራ ጋር የተያያዙ የጤንነትና የደህንነት አጠባበቅ ጉዳዮችን የሚመለከት ሲሆን፣ ዓላማውም የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት በመጠበቅ የሥራ ብቃት ማጐልበት፣ የሥራ ቦታን ለሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት በሚስማማ መልኩ ማዘጋጀት፣ ማደራጀት፣ ማሻሻልና መጠበቅ እን ዲ ሁም መሥሪያ ቤቱ /ተቋሙ/ በጐ በሆነ ማህበራዊ ሕይወት ላይ ተመስርቶ አመርቂ የሥራ ውጤት እንዲ ያስመዘግብ ማብቃት ነው፡፡

የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀፅ 47-56 ተደንግጓል፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው የተሻሻለው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የሥራ ል ብስና መሣሪያ ዝግጅትና አሰጣጥ መመሪያ በጠባቡ በሥራ ልብስና መሣሪያዎች አፈ ቃቀድና አሰጣጥ ላይ ብቻ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ከዚ ህ ሰፋ ባለ ሁኔታ ሳይንሳዊ ፅንሰ ሀሳቦች ላይ ተመስርቶ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ካለመሆኑም ባሻገር በአዋጁ የተገለፁትን ድንጋጌዎች ለመፈፀም የሚያስችል አይደለም፡፡

ስለዚህ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀፅ 1/ለ/ መሥሪያ ቤቶች የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን ፍላጐት ለሠራተኞች እንዲ ያቀርቡና ስለአጠቃቀማቸው መመሪያ እንዲ ሰጡ በተደነገገው መሠረት ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክ ፍ ል 1

## 2. ጠቅላላ

### 2.1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ''የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥናትና አፈቃቀድ አፈፃፀም መመሪያ'' ተብሎ ሊ ጠቀስ ይችላል፡፡

### 2.2 ትርጉም

2.2.1 በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 መሠረት፡-

ሀ/ 'ሠራተኛ'' ማለት በአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ ነው፡፡

ለ/ ''የመንግሥት መሥሪያ ቤት'' ማለት በአንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ሆኖ የሚኒ ስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፡፡

ሐ/ ''በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት'' ማለት በአንቀፅ 47/1/ ላይ እንደተደነገገው በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡

መ/ ''በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ'' ማለት በአንቀፅ 47/2 ላይ እንደተደነገገው የመንግሥት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

ሠ/ ''በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ'' ማለት በአንቀፅ 47/3/ ላይ እንደተደነገገው የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሰራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም።

ረ/ ''የአካል ጉዳት'' ማለት በአንቀፅ 49 ላይ እንደተደነገገው የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው።

ሰ/.''ጊዜያዊ የአካል ጉዳት'' ማለት በአንቀፅ 50 ላይ እንደተደነገገው ሠራተኛው ሥራውን ለተወሰነ ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን እንዳይችል የሚያደርገው የአካል ጉዳት ነው።

ሸ/ ''ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት'' ማለት በአንቀፅ 51 ላይ እንደተመለከተው ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ የመሥራት ችሎታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው።

ቀ/.''ዘላቂ ሙሉ የአካል ጉዳት'' ማለት በአንቀፅ 52 ላይ እንደተመለከተው ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው።

በ/ ''ኤጀንሲ'' ማለት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ነው።

2.2.2 በ ዚህ መመሪያ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር

ሀ/ ''የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች'' የሚባሉት ሠራተኛው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከጤና ጠንቆችና አደጋዎች እራሱን ለመከላከል የሚለበሱ፣ የሚደረጉ፣ የሚታሠሩ፣ የሚጠለቁ ወይም በጆሮዎች ውስጥ የሚሸጎጡ /የሚወተፉ/ የሥራ መሣሪያዎች ወይም የሥራ ልብሶች ናቸው።

ለ/ ‘’የሥራ አካባ ቢ ደህንነት /Occupational Safety /’’ ማለት አንድ ሠራተኛ በሥራ አካባቢ ው በሚገለገልባቸው የሥራ መሣሪያዎችና በሚከተላቸው የአሠራር ዘዴዎች ምክንያት ሊ ገጥሙት የሚችሉ አደጋዎችን የሚመለከት ነው::

ሐ/ ‘’የሥራ አካባ ቢ ጤንነት/ Occupational Health/’’ ማለት ሠራተኛው ከሥራ አካባቢ ው ወይም ከተመደበበት የሥራ መደብ ባህርይ ሊመነጩ የሚችሉና በጤንነት ላይ ጉዳት ሊ ያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚመለከት ነው::

መ/ ‘’የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት/ Occupational Safety and Health/’’ አጠባበቅ ማለት፡-

- የሠራተኞችን አካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ ደህንነታቸውን መንከባከብና ማሳደግ፣
- በሥራቸው ምክንያት ጤንነታቸው እንዳይጓደል መጠበቅና መከላከል፣
- ሠራተኞችን ከተፈጥሯዊ አካላቸው /Physical/ እና አዕምሮአቸው /Mental/ ጋር በተጣጣመ መልኩ መድቦ ማሠራትና መከታተል

ነው::

ሠ/ ‘’የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ‘’ ማለት ተጠሪነቱ ለሰው ሀብት ሥራ አመራር /HRM/ ሆኖ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ከሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ጥያቄዎች የሚያጠናና የውሳኔ /የመፍትሔ/ ሀሳብ የሚያቀርብ በአጠቃላይ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት እንዲ ጠበቅ የሚጥር /የሚያግዝ/ ባለሙያ ነው::

## 3. <u>የሥራ አካባቢ ደህንነት እና ጤንነትን ለመጠበቅ መፈፀም የሚገባቸው ዋና ዋና ተግባራት</u>

### 3.1 እያንዳንዱ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት፣

ሀ/ ከሥራ የሚመነጩ አደጋዎች እና በሽታዎችን መከላከል፣ ስለመሥሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ ስለቢሮዎችና የሥራ መሣሪያዎች እንዲሁም ሠራተኞች በሥራ ላይ እያሉ በሕይወትና ጤንነት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ለከፍተኛ አደጋ የመጋለጥ እና ለሠራተኞች ጤንነት መጓደል ምክንያት የሚሆኑትን ለማስቀረት የውስጥ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

ለ/ ስለ ሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ ለሠራተኞች ሥልጠና እን ዲሰጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ለሥራው አስፈላጊ የሆነ በጀት ይይዛል፡፡

ሐ/ በሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ዙሪያ ወቅታዊና የተሟሉ የመከላከያ መሣሪያዎች ዝርዝር፣ በሥራ ላይ የደረሱ አደጋዎችን ዓይነትና መጠን፣ በየጊዜው የተወሰዱ እርምጃዎችን የሚገልጹ መረጃዎች እንዲሰባሰቡ ያደርጋል፡፡

መ/ የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ በሥራ ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውንና እንዲ ሁም ሌሎች የሥራው ባህርይ ባስከተለው ህመም የተጐዱ ሠራተኞች በሐኪም የተረጋገጠ ማስረጃ ሲያቀርቡ ተገቢውን የሥራ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡

ሠ/ ሠራተኛው በሥራው ላይ ስለሚያጋጥመው የሥራ ላይ አደጋዎች እና የጤና ጠንቆችን የመከላከያ ዘዴዎች በሚገባ እንዲገነዘብ ግልጽና የተሟላ የሥራ መመሪያ እና መረጃ በመስጠት በሥራ ላይ ያውላል፡፡

ረ/ ሠራተኞች ሥራቸውን ሲ ያከናውኑ ራሳቸውን ከአደጋ የሚጠብቁበት ተገቢ፣ ምቹና በቂ የሆነ የአደጋ መከላከያ መሣሪያ በወቅቱ ያቀርባል፡፡

ሰ/ ተጠሪነቱ ለመ/ቤቱ የሰው ሀብት ሥራ አመራር ኃላፊ የሆነ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ባለሙያ ይመድባል፡፡

ሸ/ የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ለሚመለከተው ሠራተኛ በማቅረብና በመስጠት በተግባር ላይ እንዲ ውሉ ያደርጋል፡፡

ቀ/ ከሠራተኛው የሚቀርቡ የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ቅሬታዎችንና ጥቆማዎች በአግባቡ ተጣርተው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያደርጋል፡፡

3.2 <u>የመሥሪያ ቤቱ የሰው ሀብት ሥራ አመራር ኃላፊ</u>

ሀ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የቅርብ ክትትል የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት እንደ አንድ ዋና የሥራ ኃላፊነት በመውሰድ አመራር ይሰጣል፡፡

ለ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ አሰራሩን በየወቅቱ በመከታተልና በመገምገም የማሻሻያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

ሐ/ ለሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች መሟላታቸውን እና ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

መ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መረጃ በመያዝ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፡፡

ሠ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን የተመለከቱ ጉዳዮች በባለሙያ ተጠንተው ሲ ቀርቡለት ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ረ/ በሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ዙሪያ ከሠራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ወይም ጥቆማዎችን ተቀብሎ የማጣራቱን ተግባር እንዲያከናውን ለባለሙያው ይመራል፣ ከባለሙያ በሚቀርበው ሪፖርት ላይ ውሣኔ ይሰጣል፣ ወይም እንደአስፈላጊ ነቱ ለበላይ ኃላፊ በማቅረብ ሲወሰን እንዲ ፈፀም ያደርጋል::

ሰ/ የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ሥራን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ከመሥሪያ ቤቱ ዓመታዊ የበጀት ፍላጐት ጋር በማቀድ ሥራ ላይ ያውላል::

ሸ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ ከኤጀንሲው እና አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሥልጠና ዕቅድ እያዘጋጀ ሠራተኞች እንዲሰለጥኑ ያደርጋል::

ቀ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ ከኤጀን ሲው ለሚመጡ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ተቆጣጣሪዎች ሥራቸውን በአግባቡ እንዲ ያከናውኑ ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣ ከቁጥጥር በኋላ የሚሰጡትን የማሻሻያ ምክሮችንም በተግባር ያውላል::

## 3.3 <u>የመንግሥት ሠራተኛ ግዴታ</u>

ሀ/ የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ ሕጐችን እና መመሪያዎችን ያከብራል::

ለ/ የራሱን ወይም የሌሎችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የተሰጡትን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች በአግባቡ በጥቅም ላይ ያውላል::

ሐ/ የሥራ ላይ አደጋ ወይም የጤንነት ችግር ሊያደርስ ይችላል ብሎ ያመነውንና በራሱ ሊያስወግደው ያልቻለውን ማንኛውንም ሁኔታ ወይም

ስጋት ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ኃላፊው፣ ወይም ለባለሙያው ወይም ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

መ/ መሥሪያ ቤቱ በየጊዜው የሚያወጣቸውን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መመሪያዎችን ይከታተላል፣ በሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይም ይሳተፋል፡፡

ሰ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ በየጊዜው ቁጥጥር ከሚያደርጉ የኤጀንሲ ው ተቆጣጣሪዎች ለሚቀርብለት ጥያቄ መረጃና መልስ ይሰጣል፡፡

## 3.4 <u>የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ባለሙያ /Occupational Safety and Health officer/ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነት</u>

የባለሙያው ተጠሪነት ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ኃላፊ ሆኖ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ. የሥራ ቦታዎች መሣሪያዎች እና የአሠራር ዘዴዎች በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለ. ሠራተኞች የሚሠሩት ሥራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው አደጋ እንዲሁም በጤንነት ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ ስለሚያስፈልገው ጥንቃቄ ተገቢውን ሥልጠና ለሠራተኞች ይሰጣል፡፡

ሐ. የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን አጥንቶ ያቀርባል፣ ሲ ፈቀድም ሥራ ላይ እን ዲውል ያደርጋል፡፡

መ. በሥራ ላይ የደረሱ አደጋዎችንና በሽታዎችን በተመለከተ አስፈላጊው እርምጃ በወቅቱ እን ዲወሰድ ያደርጋል፣ መረጃዎችንም መዝግቦ ይይዛል፡፡

ሠ. በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችንና አደጋዎችን ከነመንስኤዎቻቸው አጥንቶ የመከላከያ እርምጃዎች /Preventive mechanism/ እንዲወሰዱ ያደርጋል፣ ለኃላፊውም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ረ/ በሥራ ቦታዎች HIV/AIDSን ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ይፈጽማል፣ ያሰፈጽማል፡፡

ሰ/ በሥራ ቦታ ድንገተኛ አደጋ በሚያጋጥምበት ጊ ዜ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አደጋ የደረሰበት ሠራተኛ ወደ ጤና ተቋማት እን ዲ ደርስ ያደርጋል፡፡

ሸ/ የመሥሪያ ቤቱ የሠራተኛ ክበብ እና የመፀዳጃ ቤቶች ደህንነትና ጤንነት የተሟላ መሆኑን በየጊ ዜው ይቆጣጠራል ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

4. <u>የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች አጠናን ስልት</u>

የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ባለሙያ

ሀ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ሲያጠና የሥራ መደቦች ዓይነት ብዛት እና ሌሎችም አግባብነት ያላቸውን መግለጫዎችና ፍሬ ነገሮች በቅድሚያ በማጣራት ይመዘግባል፡፡

ለ/ ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ እንደሥራው ጠባይ ለሠራተኛው ደህንነት፣ ጤንነት እና ንጽህና ሲባል መከላከያ መሣሪያዎቹና ቁሳቁሶቹ በእርግጥ ለሥራው ማስፈለጋቸውን ያረጋግጣል፡፡

ሐ/ ለሠራተኛ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የሚያገለግሉ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ያስፈለጉበት ምክንያት ወይም ሥራው ያለ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ሊሠራ የሚችልበት ሁኔታ ካለ ያጣራል፡፡

መ/ ውስብስብ ወይም ግልጽ ያልሆኑ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥያቄ ሲ ቀርብ ሥራው በሚገኝበት አካባቢ በመገኘት የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በማነጋገር አጥጋቢ ምላሽ ይሰጣል፡፡

ሠ/ የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈ ቃቀድ ሂደት ውስጥ ለሥራውና ለሠራተኛው ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

ረ/ የሥራ ጉብኝት የሚደረግበትን የሥራ መደብ ተግባርና ኃላፊነት በማጥናት ሥራው የሚያስከትለው አደጋና የጤንነት ችግር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ይረዳል፡፡

ሰ/ በጉብኝቱ ወቅት ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችን ይለያል፣ ሁኔታዎችን በአግባቡ ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎችንም ያዘጋጃል፡፡

ሸ/ የሥራ ጉብኝት የሚደረግበትን ቀን ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ይወሰናል፣ የቀጠሮውን ቀንና ሰዓት አክብሮ በሥፍራው ይገኛል፡፡

በ/ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጋር በመሆን የጉብኝቱን ዓላማ ይገልጻል፡፡

ተ/ ሥራው በሚከናወንበት አካባቢ በመገኘት ቃለመጠይቅ በማቅረብ ስለሥራው ይረዳል፡፡

ቸ/ በቃለመጠይቅ ወቅት ግልጽና ቀላል ቋንቋ ይጠቀማል፣ በጉብኝትና በቃለመጠይቅ ጊዜ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እየመረጠ በማስታወሻ ይይዛል፡፡

ከ/ ባለሙያው ሪፖርት አጠናቅሮ የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ለኃላፊው ያቀርባል፣ ኃላፊው በሚሰጠው ውሳኔ ወይም አስተያየት መሠረት እንዲ ፈፀም ያደርጋል፡፡

### 5. የውሳኔ አሰጣጥ

የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ አግባብነት ያለው የአጠናን ስልት በመጠቀም ያገኛቸውን መረጃዎች በመተንተን የሥራ አካባበ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች አጥንቶ ለሰው ሀብት ሥራ አመራሩ ኃላፊ ሲ ያቀርብ ኃላፊው ይወስናል፣ ወይም የውሳኔ ሀሳቡን ያፀድቃል፣ ወይም ጉዳዩ እንደገና እንዲ ጠና ወይም እንዲ መረመር ያዛል፡፡

## ክፍል 2

### 6. ልዩ ትኩረት ስለሚሰጣቸው ሠራተኞች

እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፡-

6.1 አንድ ነፍሰጡር ሴት ከእርግዝና በፊት ትሠራበት የነበረው የሥራ መደብ በጤንነቷ ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ በሀኪም ከተረጋገጠ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ ወደሌላ የሥራ መደብ ተዛውራ እንድትሠራ ያደርጋል፡፡

6.2 በሥራ ምክንያት በመጣ አደጋ የአካል ጉዳተኛ የሆነ የመንግሥት ሠራተኛ ድጋሚ ጉዳት እንዳይደርስበት የሥራ አካባቢ ወይም ቢሮው በደህንነቱ ወይም በጤንነቱ ላይ አደጋ የማያስከትልና ለእንቅስቃሴ ምቹ እን ዲሆን ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል 3</u>

### 7. <u>የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መረጃዎች ስለመመዝገብና ስለመያዝ</u>

እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት ከመመሪያው ጋር አባሪ በተደረጉት ሠንጠረዥ ሀ፣ ለ፣ ሐ እና መ ላይ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፡፡

### 8 <u>የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መረጃዎችን ለኤጀንሲው ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀፅ 60/2/ መሠረት እያንዳንዱ መሥሪያ ቤት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በሚቀጥለው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ወር /ሐምሌ/ ውስጥ ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ መ እና ሠ ላይ መረጃዎቹን ሞልቶ ለኤጀንሲው ይልካል፡፡

## <u>ክፍል 4</u>

### 9. <u>አውጭው ባለሥልጣን</u>

በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 48/3/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 10. <u>የተሻረ መመሪያ</u>

ሰኔ 10 ቀን 1992 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ57/16/325 በተጻፈ ሰርኩላር የተላለፈው የተሻሻለው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የሥራ ልብስ እና መሣሪያ ዝግጅትና አሰጣጥ መመሪያ ተሽሮአል፡፡

## 11. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው በአዋጅ ቁጥር 515/99 በሚተዳደሩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ብቻ ነው፡፡

## 12. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 13. አባሪዎች

13.1 የሥራ አካባ ቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች መመዝገ ቢያ /ሠንጠረዥ ሀ/

13.2 የህክምና ሪኮርድ መመዝገቢ ያ /ሠንጠረዥ ለ/

13.3 በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት መመዝገ ቢያ /ሠንጠረዥሐ/

13.4 በሥራ ምክንያት የደረሱ አደጋዎችና በሽታዎች ሪፖርት መላኪያ /ሠንጠረዥ መ/

**ሠንጠረዥ ሀ**

**<u>የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች መመዝገቢያ</u>**

**የመሥሪያ ቤቱ ስም -------------------------**

| ተራ ቁጥር | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የሚያስፈልገው ቁሳቁስ ዓይነት/መጠሪያ | የሚሰጠው አገልግሎት | የተፈቀደበት ቀን | ብዛት | አጭር መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |

መረጃውን የሞላው ባለሙያ

**ሠንጠረዥ ለ**

## <u>የህክምና መመዝገቢያ</u>

**የመሥሪያ ቤቱ ስም ---------------------------**

| ተራ ቁጥር | የሠራተኛ ስም ከነአያት | ዕድሜ | ጾታ | ሥራው /ሙያው/ | የበሽታው አይነት | የበሽታው መንስኤና ዕለት | | የህክምና ምርመራ ግኝት | የተደረገ /እየተደረገ ያለው የህክምና ዓይነት | | በሥራ ላይ ለደረሰ ህመም የህክምና ወጪ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዕለት/ቀን | መንስኤው | | መኝታ | ተመላላሽ | በህመም ፈቃድ የተከፈለ ደመወዝ | የህክምናና መድህኒት ወጪ |
| | | | | | | | | | | | | |

**የህክምናና መድህኒት ወጭዎች ማለት በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 53/1/ የተገለጸው ነው።**

**በህመም ምክንያት የተከፈለ ደመወዝ ማለት በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 53/2/ የተገለጸው ነው።**

**ሠንጠረዥ ሐ**

## <u>በሥራ ላይ የደረሰ ጉዳት መመዝገቢያ</u>

**የመሥሪያ ቤቱ ስም ---------------**

| ተራ ቁጥር | የሠራተኛው ስም ከነአባት | አደጋው የደረሰበት ሠራተኛ | | | አደጋው የደረሰበት | | | የአደጋው ዓይነት | የአደጋው ምክንያት | የተወሰደ እርምጃ | የተጎዳው ሰው ከሥራ ታውኮ የቀረበት ቀን ብዛት | ከሥራ ላይ በመጣ ጉዳት ምክንያት ስለሚሰጥ ህክምና ወጭዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕድሜ | ጾታ | ሥራው/ ሙያው/ | ዕለት | ቀን | ሰዓት | | | | | ለህክምና ፈቃድ የተከፈለ ደመወዝ | የህክምና መድሀኒት ወጪ |
| | | | | | | | | | | | | | |

የህክምናና መድሀኒት ወጭዎች ማለት በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 53/1/ የተገለጸው ነው።

በህመም ምክንያት የተከፈለ ደመወዝ ማለት በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 53/2/ የተገለጸው ነው።

መረጃውን የሞላው ባለሙያ

**ሠንጠረዥ መ**

## በሥራ ምክንያት የደረሱ አደጋዎችና በሽታዎች ሪፖርት መላኪያ

**የመሥሪያ ቤቱ ሥም** -------------------------------------

| ተራ ቁጥር | የአደጋው/የበሽታው ዓይነት/ጉዳት | ፃታ | አደጋው/በሽታው የተከሰተበት የሥራ መደብ | አደጋው በሽታው የደረሰበት | | በአደጋው የበሽታው ምክንያት | | ለሕክምና መድሀኒት የወጣ ወጪ | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ቀንና ዓ.ም | ምክንያት | የተሰጠ ፈቃድ ቀን ብዛት | የተከፈለ ደሞዝ መጠን | | |
| | | | | | | | | | |

**በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀፅ 60/2/ መሠረት**
**መረጃውን የሞላው ባለሙያ**

ሠንጠረዥ ሠ

## በመሥሪያ ቤቱ የተፈቀዱ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ዝርዝር ሪፖርት ማቅረቢያ

የመሥሪያ ቤቱ ስም ---------------------------------------

| ተራ ቁጥር | የሥራ መደብ መጠሪያ | ለሥራ መደቡ የተፈቀደ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ዝርዝር | ለመሣሪያዎች እና ቁሳቁሶች የወጣ | | ተጨማሪ መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብር | ሣ | |
| | | | | | |

በአዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀፅ 60/2/ መሠረት